# ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
*2016/18*

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

---

## ፍሎራይድ ሲበዛ በጥርስና በአጥንት ላይ ጉዳት ያደርሳል፡-የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲና የኢትዮጵያ መንግሥት በጋራ የፍሎራይድ መቀነሻ ቴክኖሎጂ ማዕከል ከፈቱ

ሞጆ፣ኦሮሚያ ክልል፣ኢትዮጵያ፣ሚያዝያ 6 ቀን 2008 ዓ.ም.፡- የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ( USAID) ዳይሬክተር ዴኒስ ዌለር እና የውሃ የመስኖና የኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶኤታ ክቡር አቶ ከበደ ገርባ በዛሬው ዕለት የፍሎራይድ ማጣሪያዎችን የሚያመርት አዲስ ፋብሪካ በጋራ መርቀው ከፈቱ፡፡ ፋብሪካው የተገነባው የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ለኦሮሞ ራስ አገዝ ድርጅት ባደረገው ድጋፍ ሲሆን፤ ፋብሪካው በኢትዮጵያው የስምጥ ሸለቆ አካባቢ ለሚገኙ ማህበረሰቦች የተለያዩ የፍሎራይድ መቀነሻ ምርቶችንና አገልግሎቶችን ያቀርባል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ፍሎራይድ የተሰኘው ንጥረ ነገር በውሃ ውስጥ መኖሩ ጥሩ ቢሆንም፤መጠኑ -ሲበዛ ግን ፍሎሮሲስ ለሚባል የጤና ችግር ይዳርጋል፡፡ ፍሎሮሲስ በተለይም በጥርስና በአጥንት ላይ ጉዳት በማድረስ የሰዎችን ጤና ያውካል፡፡ በተለይም ዕድሜአቸው ከስምንት ዓመት በታች የሆነና ገና ጥርስ ያላበቀሉ ህጻናት የችግሩ ግንባር ቀደም ተጠቂ ሲሆኑ፤ፍሎራይድ የበዛበትን ውሃ ለረጅም ጊዜ የሚጠጡ ህጻናት ለአጥንት መሳሳት ችግር ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡ በአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ድጋፍ የተገነባው ይህ ፋብሪካ ከአካባቢው ከሚገኝ የአጥንት ከሰልና እምብዛም ወጪ የማያስወጡ ኬሚካሎችን በመጠቀም የፍሎራይድን መጠን ለመቀነስ የሚረዱ ምርቶችን ያቀርባል፡፡ ፋብሪካው የሚያመርታቸው ምርቶችን እስከ አምስት ጊዜ ድረስ በድጋሚ መጠቀም የሚቻል ሲሆን፤የአገልግሎት ጊዜያቸው ሲያበቃም ለአካባቢ ጎጂ ያልሆነ የፎስፌት ማዳበሪያ በመሆን አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ዳይሬክተር ዴኒስ ዌለር ባደረጉት ንግግር፡-“ይህ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ባደረገለት ድጋፍ በኦሮሞ ራስ አገዝ ድርጅት የተገነባውና በሀገሪቱ በዓይነቱ የመጀመሪያው የሆነው ፋብሪካ የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ የፍሎራይድ ማጣሪያዎችን ያመርታል፡፡ ይህም በስምጥ ሸለቆ አካባቢ በሚገኝ የከርሰ ምድር ውሃ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የቆየውን ከተገቢው መጠን በላይ የሆነ የፍሎራይድ መጠንን ችግር ለመቅረፍ ወቅታዊ እርምጃ ነው” ብለዋል፡፡

የኦሮሞ ራስ አገዝ ድርጅት በመጀመሪያ በአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ድጋፍ ለተቋቋሙና በምሥራቅ ሸዋ ዞን ባሉ አራት ወረዳዎች የሚገኙ 12 የማህበረሰብ የፍሎራይድ ማከሚያ ማዕከላት የውሃ ማጣሪያዎቹን የሚያከፋፍል ሲሆን፤ይህንን ንጹህ ውሃ የሚጠቀሙ ተጠቃሚዎች በጣም አነስተኛ የሆነ ክፍያ ይጣልባቸዋል፡፡ ከሚሰበሰበው ገንዘብም የተወሰነው ድርሻ እንደ አስፈላጊነቱ ምትክ የሚሆኑ ማጣሪያዎችን በመግዛት ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

ለወደፊቱም ፋብሪካው በአፋር፣በኦሮሚያ እና በደቡብ ክልሎች ለሚገኙ ተመሳሳይ የፍሎራይድ ችግር ላለባቸው ወረዳዎች እነዚህን የውሃ ማጣሪያዎች ያቀርባል፡፡

###

*For more information on this project, contact Mr. Esayas Samuel, Project Manager, OSHO, Mobile: 0911-436871 or esayassam@yahoo.com. For more information on USAID: Visit us on Facebook: www.facebook.com/usaidethiopia, follow us on Twitter @USAIDEthiopia or go to www.usaid.gov/ethiopia*